# ደንብ

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**

*ተዛማጅ ፅሁፎች፦* ACA, ACF, JFA, JFA-RA, JHC, JHC-RA, JHF, JHF-RA

*ሀላፊነት ያለው ቢሮ፦* የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ፤ ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ፤ የስራ ሂደት ሀላፊ፤ የት/ቤት ድጋፍ እና ደህንነት ሀላፊ፤ የዲስትሪክት ስራ ሂደቶች ሀላፊ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) Title IX ተማሪዎች ፆታዊ ትንኮሳ ምርመራ

I. **ዓላማ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) Title IX ተማሪዎች ፆታዊ ትንኮሳ ጋር በተገናኘ ለሚቀርቡ አቤቱታዎች በፍጥነት ምላሽ ለመስጠት የአሰራር ቅደም ተከተሎችን ማቅረብ

II. **ትርጉም**

A. ፆታዊ በደል እና ፆታዊ ትንኮሳ የሚባሉት ስያሜዎች የሚኖራቸው ትርጉም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACF፣ የተማሪዎች ፆታዊ በደል እና ፆታዊ ትንኮሳ ላይ በተሰጠው ትርጓሜ መሰረት ነው።

B. የስራ ቀን ማለት ከቅዳሜ፣ እሁድ፣ ወይም ሌላ ህጋዊ በአል ውጪ የሆነ ቀን ነው፣ ይሄውም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማዕከላዊ ቢሮዎች ለስራ ክንውን ክፍት የሚሆኑባቸው ቀኖች ናቸው።

III. **ቅደም-ተከተል**

A. ፆታዊ በደል እና ፆታዊ ትንኮሳ ተገቢ ያልሆነ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACF፣ የተማሪዎች ፆታዊ በደል እና ፆታዊ ትንኮሳ የተሰኘውን ፖሊሲ መጣስ ነው። ይሄውም ድርጊቱ የተከናወነው ከሁለት አንዱ ፆታ ባላቸው ተማሪዎች ሌላ ተቃራኒ ጾታ ወይም ተመሳሳይ ፆታ ያላቸው ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ላይ የሚደረግ ጾታዊ ትንኮሳ/ጥቃት ነው።

B. የት/ቤት ሰራተኞች እና በዲስትሪክት የስራ ሂደት ቢሮ፣ በተማሪ ደህንነት እና ማክበር ክፍል የሚገኙ ሰራተኞች፣ ከፆታዊ በደል እና ፆታዊ ትንኮሳ ጋር ተዛማጅ ለሆኑ ጉዳዮች መፍትሄና ድጋፍ ለመስጠት፣ እንዲሁም ለተማሪዎች እና ለወላጆች መመሪያ መስጠት ይችላሉ።

C. የተማሪ ደህንነት እና ሥነ ስርአት አስከባሪ ክፍል የዚህን ደንብ አፈፃፀም በሚከተለው መንገድ ያስተባብራል፦

1. ለተማሪዎች ተደራሽ በሆኑ የድጋፍ እርምጃዎች ላይ እና ፆታዊ በደል እና ፆታዊ ትንኮሳን በሚመለከት ማመልከቻ/ሪፖርት ማድረጊያ እና አሰራር ሂደቶች ላይ የምርመራ መረጃዎችን ማሰራጨት።

2. ፆታዊ በደል እና ፆታዊ ትንኮሳን ለመመርመር እና የቀረቡ ክሶችን ለመፍታት የስልጠና ፕሮግራሞችን እና መመሪያዎችን ዝግጅት መደገፍ።

3. በፆታዊ በደል እና ፆታዊ ትንኮሳ፣ በጤና ግንዛቤ ክህሎቶች (ለምሳሌ፦ ከሌሎች ጋር ግንኙነት፣

ራስን-መጠበቅ፣ ስለ ራስ ወይም ስለ ሌሎች ማቀንቀን) ላይ የተማሪ ግንዛቤን ለማዳበር፤እና ስለ ግላዊ ሰውነት ደህንነት አጠባበቅ ስልቶች ላይ ለእድሜ-ተገቢ የሆነ ስርዓተ ትምህርት እና ለተማሪ-የሚቀርቡ ግብዓቶች ዝግጅት ላይ ድጋፍ መስጠት።

4. በ MCPS ውስጥ የሚፈፀም የተማሪ ፆታዊ በደል እና ፆታዊ ትንኮሳ አቤቱታዎችን ምርመራ፣ሰነድ አያያዝ በተመለከተ ለት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ማሳወቅና ማመቻቸት።

5. ፆታዊ በደል እና ፆታዊ ትንኮሳ አቤቱታዎችን መከታተል።

6. የሪፖርቶች፣ የአቤቱታዎች፣ እና ይሄንን ተከትሎ የሚመጣ አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ፣ የሚስጥራዊነት መስፈርቶችን በማክበር፣ የሰነድ-አያያዝ ስርዓትን ጠብቆ ማስቀጠል።

7. ፆታዊ በደል እና ፆታዊ ትንኮሳ ሪፖርቶች ላይ ለቦርድ የሩብ አመት ሪፖርት ማዘጋጀት፣ ይሄም የሚያካትተው–

   a) የተፈጠሩ ክስተቶች ብዛት እና አይነት፤

   b) የአቤቱታ እና የመፍትሄ-ሂደት ግምገማዎች እና ማሻሻያዎች፤

   c) የስልጠና ስታትስቲክስ እና መርህ ግብሮች፤

   d) በሁሉም MCPS ት/ቤቶች፣ ቢሮዎች፣ እና የስራ ቦታዎች ያሉትን የስራ አካባቢዎች/ሁኔታዎች ላይ ቀጣይነት ያለው ግምገማ፤ እና

   e) የቦርድ ፖሊሲ ACF፣ የተማሪዎች ፆታዊ በደል እና ፆታዊ ትንኮሳ እና የቦርድ ፖሊሲ ACI፣ የሰራተኞች ፆታዊ ትንኮሳ በስኬታማነት ለመተግበር ጠቃሚ የሆኑ በ MCPS የታቀዱ እና የተከናወኑ/የተሰሩ ሌላ ተግባራት።

## IV. የሪፖርት አቀራረብ ሂደቶች

A. ፆታዊ በደል እና/ወይም ፆታዊ ትንኮሳ ያጋጠማቸው ወይም የተመለከቱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች፣ ወይም የእነሱ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ለዳይሬክተራቸው ወይም ሌላ MCPS ሰራተኛ ይሄን አይነቱን ድርጊት ማመልከት አለባቸው፣ ያሳወቁትም ግለሰብ በማመልከት/ሪፖርት በማደርግ እና በምርመራ ሂደቶች ላይ ምን መደረግ እንዳለበት ይመራቸዋል እና ማግኘት የሚችሉትን የድጋፍ እርምጃዎችን ያሳውቋቸዋል።

1. ሪፖርቱ ለማንኛውም የሰራተኛ አባል በቃል ወይም በፅሁፍ ሊቀርብ ይችላል። የሰራተኛ አባሉም ተማሪን፣ ወላጅን ወይም አሳዳጊን ለዳይሬክተር ወይም ለተወካይ ሪፖርት ማደረግ ላይ ወይም MCPS ቅፅ 230-35፣ አካላዊ ጥቃት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራሪያ ሪፖርት ማድረጊያ ቅፅ መሙላት ላይ ያግዛቸዋል/ታግዛቸዋለች።

2. MCPS ቅፅ 230-35 በተማሪ፣ በወላጅ፣ በአሳዳጊ ወይም በተማሪ የቅርብ ዘመድ፣ ወይም በት/ቤት ሰራተኛ አባል መሞላት ይችላል። ተሞልቶ ካለቀ በኋላ፣ ቅጹ ለት/ቤት ዳይሬክተር ወይም ተወካይ ወይም ለተማሪ ደህንነት እና ሥነ ሥርዓት ማስከበር ክፍል ማስገቢያ ሳጥን SWC@mcpsmd.org ገቢ ይደረጋል።

3. Title IX ፆታዊ ትንኮሳ ሪፖርት በተጨማሪም ሊደረግ የሚችለው Title IX ፆታዊ ትንኮሳ ማስገቢያ ሳጥን Title IX@mcpsmd.org ገቢ መደረግ ይችላል።

4. ለሰራተኛ አባል ፆታዊ ትንኮሳ ሪፖርት ሲደረግ፣ እርዳታ የሚ(ምት)ሰጠው የሰራተኛ አባል MCPS ቅፅ 0109.22 EGPS ስለ ተማሪ ፆታዊ ትንኮሳ መደበኛ አቤቱታ ማቅረቢያ ቅጽ፣ Title IX ስለ ማግለል መደበኛ አቤቱታ በመጠቀም ሪፖርት እንዲያ(ድታ)ቀርብ ያግዛል/ታግዛለች።

B. የተፈጠረ ክስተትን ሪፖርት በማድረግ ወይም ተፈጥሯል በተባለው ክስተት ምርመራ ላይ በሚሳተፍ ወይም በሚተባበር ግለሰብ ላይ ምንም አይነት ያልተገባ እርምጃ አይኖርም።

C. MCPS የምርመራውን ሚስጠራዊነት ይጠብቃል፣ ይሄም ተግባራዊ ከሚሆኑ ህጎች እና የዚህ አይነት አቤቱታዎችን ከመመርመር እና መፍትሄ ከመስጠት አኳያ MCPS ሀላፊነት ጋር ተስማሚ በሆነ መልኩ ነው።

V. **ምርመራ**

A. የፆታዊ በደል አቤቱታ ምርመራ

1. የፆታዊ በደል አቤቱታ ምርመራ የሚካሄደው MCPS ደንብ JHF-RA፣ አካላዊ ጥቃት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት፣ MCPS ቅፅ 230-36፣ አካላዊ ጥቃት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራሪያ ክስተት የት/ቤት ምርመራ ቅፅ በመጠቀም ነው።

2. ማድረግ በሚቻለው ፍጥነት በድርጊቶቹ ላይ ተገቢ እርምጃ ይወሰዳል እና ለተማሪ ደህንነት እና ሥነ ስርአት ማስከበሪያ ክፍል ሪፖርት ይደረጋል።

B. Title IX ፆታዊ ትንኮሳ አቤቱታ ምርመራ

የዩ.ኤስ. ትምህርት ድፓርትመን 2020 መመሪያ ስለ መደበኛ የፆታዊ ትንኮሳ አቤቱታ Title IX በፌደራል መጠቀም የተከለከሉ የምርመራ ሂደቶችን ይገልጻል።

1. Title IX ፆታዊ ትንኮሳ አቤቱታ ምርመራ እንዲደረግ ለመጠየቅ፣ ተማሪ ወይም የተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ MCPS ቅፅ 0109.22 EGPS፣ Title IX ስለ ማግለል መደበኛ አቤቱታ መሙላት፣ ወደ Title IX አስተባባሪ TitleIX@mcpsmd.org ማቅረብ አለባቸው።

2. Title IX ፆታዊ ትንኮሳ መደበኛ አቤቱታ በሚከተሉት የፌደራል መጠቀም የተከለከሉ እና የተፈቀዱ ሁኔታዎች መሰረት ይከናወናል፦

   a) መደበኛ አቤቱታን በሚመለከት መደረግ የሌለባቸው ህጋዊ ግዴታዎች

      (1) Title IX አስተባባሪ መደበኛ አቤቱታን ውድቅ ማድረግ ያለበት/ባት–ሁኔታ

         (a) በመደበኛ አቤቱታ ተፈፅሟል ተብሎ የቀረበው ድርጊት ምንም እንኳን ድርጊቱ ቢረጋገጥም Title IX ፆታዊ ትንኮሳ ትርጉም/ፍቺን የማያሟላ ከሆነ፣ ወይም

         (b) ድርጊቱ የተፈጠረው MCPS የትምህርት ፕሮግራሞች/ተግባራት በሚከናወኑበት ሁኔታ ውስጥ ካልሆነ።

      (2) መደበኛ አቤቱታ ውድቅ መደረግ ያለበት ሁኔታ MCPS ደንብ JHF-RA፣

አካላዊ ጥቃት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራሪያ፣MCPS ተማሪ ስነምግባር ደንብ፣ ወይም ሌላ ተፈፃሚ የሚሆኑ ህጎች ስር የሚገኝ ድርጊትን አያስቀርም/አያካትትም።

B. መደበኛ አቤቱታን ውድቅ ማድረጊያ በግል የሚወሰን ሁኔታ

(1) Title IX አስተባባሪ መደበኛ አቤቱታን ውድቅ ማድረግ የሚ(ምት)ችለው–

(a) አቤቱታ አቅራቢው(ዋ) ወደ Title IX አስተባባሪ መደበኛ አቤቱታውን ማንሳት መፈለጉን/ጓን በፅሁፍ ከገለፀ/ች፤ ወይም

(b) መልስ ሰጪው/ዋ አሁን ላይ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተመዘገበ/ች ወይም የተቀጠረ/ች ካልሆነ፤ ወይም

(c) MCPS የቀረበው መደበኛ አቤቱታ ወይም ተፈፅሟል የተባሉት ክሶች ላይ ከውሳኔ ለመድረስ የሚያስችል በቂ ማስረጃ ከመሰብሰብ የሚያግዱ የተለዩ ሁኔታዎች ካሉ ነው።

3. መደበኛ አቤቱታ ከተቀበ(ች) እና ከገመገመ(ች) በኋላ፣ Title IX አስተባባሪ ወይም ተወካይ የክሱን የፅሁፍ ማሳወቂያ ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል/ታስተላልፋለች እና መርማሪ ይመድባል/ትመድባለች።

4. መርማሪው/ዋ ሀላፊነት መውሰድን በሚመለከት ውሳኔ ላይ ለመድረስ ማስረጃ ይሰበስባል/ትሰበስባለች። ሁሉም አካላት የምስክርነት ቃል መስጠት፣ ምስክሮችን እና ሌላ ማስረጃን ጨምሮ ለመርማሪው(ዋ) ማስረጃ ለማቅረብ እኩል እድል ይኖራቸዋል።

5. በመርማሪው(ዋ) አማካይነት በሀላፊነት የሚያስጠይቅ መደምደሚያ እስኪወሰን ድረስ በቅድሚያ የሚታሰበው ምላሽ ሰጪው አካል ተፈፀመ ለተባለው ድርጊት ሀላፊነት እንደሌለበት/ባት ተደርጎ ነው።

6. የምርመራ ሪፖርቱ ከመጠናቀቁ በፊት፣ የማስረጃ ግምገማ ጊዜ ሊኖር ይገባል፣ በዚህ ወቅትም መርማሪው/ዋ ከቀረቡት ክሶች ጋር በቀጥታ ተዛማጅ የሆነ ማስረጃን ለእያንዳንዱ አካል እና ለአማካሪዎቻቸው ይልካል/ትልካለች። እያንዳንዱ አካል የፅሁፍ ምላሽ እንዲያቀርቡ 10 ቀናት ይሰጣቸዋል።

7. ከመረጃ ግምገማ ጊዜ በኋላ፣ መርማሪው/ዋ የፅሁፍ ምላሾችን የገመግማል/ትገመግማለች እና የምርመራ ሪፖርት ረቂቅ ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች።

8. የምርመራ ሪፖርት ከተጠናቀቀ በኋላ፣ እያንዳንዱ ወገን እና አማካሪው(ዋ) ሪፖርቱን ለመመልከት እና የፅሁፍ ምላሽ ለመስጠት 10 ቀናት ይኖራቸዋል።

9. ከምርመራ ሪፖርት ግምገማ በኋላ፣ ዳይሬክተር ወይም ተወካይ የምርመራ ሪፖርቱን እና ማንኛውንም የፅሁፍ ምላሽ(ሾች) ይመዝናል/ትመዝናለች እና ምክረ ሀሳብ ወደ Title IX አስተባባሪ ያቀርባል/ታቀርባለች፣ ይሄም አካል እነዚህን ሰነዶች ለአምስት የስራ ቀናት ከገመገመ/ች በኋላ ሀላፊነት የሚወስደው ድርጊቱን የፈፀመ አካል ማን እንደሆነ ውሳኔ ያሳውቃል/ታሳውቃለች። ውሳኔው ለሁሉም ወገኖች በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ ይደርሳል።

10. ለክስ የቀረበው ድርጊት Title IX ስር *ፆታዊ ትንኮሳ* ተብሎ መመደቡ ወይም አለመመደቡ ላይ ውሳኔው የማስረጃ ተበላይነት ደረጃዎች ላይ ተመርኩዞ ይደረጋል።

C. Title IX *ፆታዊ ትንኮሳ* አቤቱታ ኢ-መደበኛ ውሳኔ

1. ሀላፊነት/ተጠያቂነት የመውሰድ ውሳኔ ከመሰጠቱ አስቀድሞ፣ ማንኛውም ወገን/አካል ለመደበኛ አቤቱታ ኢ-መደበኛ ውሳኔ እንዲሰጥ መጠየቅ ይችላል።

2. በኢ-መደበኛ ውሳኔ ላይ ተሳትፎ ማድረግ በግል ፈቃደኝነት ላይ ይወሰናል። ሁለቱም ወገኖች ለኢ-መደበኛ ውሳኔ ሂደት የግል ፈቃደኝነታቸውን የፅሁፍ ስምምነት ሊሰጡ ይችላሉ።

3. በሰራተኛ ተፈፀመ ለተባለ የተማሪ *ፆታዊ ትንኮሳ* ክሶች የቀረበ መደበኛ አቤቱታን ለመፍታት የኢ-መደበኛ ውሳኔ ሂደት ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም።

## VI. ምላሽ ሰጪ እርምጃዎች

A. አንዳንድ የ*ፆታዊ ትንኮሳ* አይነቶች የወንጀል ድርጊት ውስጥ ሊካተቱ ይችላሉ፣ ይሄም የወንጀል ቅጣቶችን ወይም የህፃናት ብዝበዛ ሊያስከትል ይችላል፣ስለዚህ ሪፖርት መደረግ ያለበት MCPS ደንብ JHC-RA፣ የህፃናት ብዝበዛ እና ቸልተኝነት ሪፖርት ማድረግ እና ምርመራ፣ እና/ወይም ከህግ አስፈፃሚ ባለስልጣናት ጋር በተደረገ የመግባቢያ ሰነድ መስፈርቶች መሰረት ይሆናል።[1]MCPS ማንኛቸውንም የውስጥ ምርመራዎችን ምርመራ ከሚያካሂዱ ከውጭ የህግ አስከባሪ ወኪል ድርጅቶች ጋር ሙሉ በሙሉ ተባባሪ በሆነ፣ እና የውጪን ምርመራ ጣልቃ በማይገባበት ወይም አደጋ በማያደርስበት መንገድ ማካሄድ አለበት።

## VII. ይግባኝ

A. *ፆታዊ በደልን* በሚመለከት የተደረገ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሊቀርብ የሚችለው MCPS ደንብ KLA-RA፣ ከህዝብ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች እና አቤቱታዎች ምላሽ መስጠት በተቀመጡት አሰራሮች መሰረት ነው።

B. Title IX *ፆታዊ ትንኮሳ* ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት

1. በዳይሬክተር ወይም በተወካይ የተደረገ ሀላፊነት/ተጠያቂነት የመውሰድ ውሳኔ ላይ ከሁለት በአንዱ ወገን በኩል ወደ Title IX አስተባባሪ ይግባኝ ሊቀርብ ይችላል።

2. በአንዱ ወገን ይግባኝ መቅረብ ያለበት ውሳኔው ከተደረገበት አንስቶ 10 የስራ ቀናት ውስጥ ነው።

3. ሀላፊነት/ተጠያቂነት መውሰድ ውሳኔ ላይ፣ ወይም የመደበኛ አቤቱታ ውድቅ ማድረግ ላይ ከሁለት በአንዱ ወገን ይግባኝ ማቅረብ የሚቻለው በሚከተሉት መስፈርቶች ላይ በመመርኮዝ ነው:-

   a) የአሰራር መዛባት የምርመራው ውጤት ላይ ተፅዕኖ ካሳደረ፤

   b) ሀላፊነት/ተጠያቂነት መውሰድን በሚመለከት የተደረሰው ውጤት ላይ ለውጥ/ተፅዕኖ ሊኖረው የሚችል ማስራጃ ሆኖ አሳማኝ በሆነ መንገድ ውሳኔው በተሰጠበት ወቅት ወይም መደበኛ አቤቱታው ውድቅ በተደረገበት ወቅት ማቅረብ የማይችል ከነበር፤

---

[1] *ሙሉ ርዕስ፡- የህግ አስፈፃሚን ተሳትፎ የሚያካትቱ ክስተቶች ላይ የሪፖርት ማድረጊያ ፕሮቶኮሎች/አሰራር ቅደም ተከተሎች በዝርዝር የተቀመጡት፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ ዲፓርትመንት እና በሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ እና በሌላ ኤጀንሲዎች መካከል የማህበረሰብ ተሳትፎ ኃላፊ ፕሮግራም እና ት/ቤት-መሰረት ላደረጉ ክስተቶች ሌላ የህግ አስፈፃሚ ምላሾችን በሚመለከት የመግባቢያ ሰነድ፣ አፕሪል 4፣ 2022። (የመግባቢያ ሠነድ)*

ወይም

c) Title IX አስተባባሪ፣ መርማሪ፣ ወይም ውሳኔ ሰጪ(ዎች) በጉዳዩ የተሰጠው ውሳኔ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር ተቃራኒ ፍላጎት/የሚጋጭ ፍላጎት ወይም መድሎ ከነበራቸው።

4. ክሱን ለመስማት የሰለጠነ ሰራተኛ ይመደባል።

5. ይግባኝ ከቀረበ፣ ክሱን የሚሰማው ሰራተኛ ለሌላኛው ወገን በፅሁፍ ያሳውቃል/ታሳውቃለች።

6. ሁለቱም ወገኖች ውሳኔውን በሚመለከት በፅሁፍ ቃላቸውን እንዲሰጡ እድል ይሰጣቸዋል።

7. የፅሁፍ አቤቱታ ከተቀበለ/ች 10 ቀናት ውስጥ፣ ክሱን የሚሰማው ሰራተኛ ማድረግ ያለበ(ባ)ት –

a) የምርመራ ሰነዶችን እና በሁለቱም ወገን በጽሑፍ የቀረቡ ማንኛውንም የክርክር ነጥቦችን መገምገም፤

b) በይግባኝ ላይ የተደረሰውን ውጤት/መደምደሚያ እና መደምደሚያው የተደረገበትን ምክንያት የሚገልፅ የፅሁፍ ውሳኔ ማቅረብ፣ ይሄም በተመሳሳይ ጊዜ ለሁለቱም ወገኖች ይላካል፤ እና

c) ለሁለቱም ወገኖች ውሳኔውን እና በቦርድ ፖሊሲ BLB፣ የይግባኝ እና ክስ የመስማት አሰራር ደንቦች፣ እና በስቴት ህጋዊ አሠራር መሠረት በውሳኔው ላይ ይግባኝ ለቦርድ 30 ቀናት ውስጥ የማቅረብ መብታቸውን ማሳወቅ።

## VIII. ግንኙነት እና የመረጃ ስርጭት

ፆታዊ በደል እና ፆታዊ ትንኮሳን የሚመለከቱ የቦርድ ፖሊሲዎች እና MCPS ደንቦች እና ህጎች ላይ በጽሑፍ የተዘጋጀ መረጃ ለሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ይሰራጫል፣ ይሄም ፆታዊ በደል እና ፆታዊ ትንኮሳ በምን መንገድ ትርጓሚ/ፍቺ እንደተሰጣቸው፣ ፆታዊ በደል እና ፆታዊ ትንኮሳ ከገጠማቸው ምን ማድረግ እንደሚችሉ፣Title IX አስተባባሪ የሚያገኙበት አድራሻ መረጃ፣ እና እርዳታ ለማግኘት እንዴት ማሳወቅ እንደሚችሉ የሚገልጽ መረጃዎችን ያካትታል።

መረጃ በተለያዩ መንገዶች ይሰራጫል፣ በዚህ ብቻ ባይወሰንም የሚከተሉትን ያካትታል—

A. የስልጠና አውደ ጥናቶች እና/ወይም የኦንላይን ትምህርት/ሞጁሎች፣

B. ብሮሹሮች/በራሪ ጽሑፎች፣

C. የማስታወቂያ ሠሌዳዎች፣

D. መተግበሪያዎች፣

E. ማስታወቂያዎች፣ እና/ወይም

F. ሌላ የብዙሃን መገናኛ መንገዶች፣ ተገቢ ከሆነ።

## IX. TITLE IX ስልጠና

A. Title IX አስተባባሪ፣ መርማሪ፣ ውሳኔ ሰጪዎች፣ የኢ-መደበኛ ውሳኔ እና የፆታዊ ትንኮሳን መደበኛ አቤቱታዎች የሚያመቻች ማንኛውም ግለሰብ ስልጠና ይወስዳሉ።

B. ስልጠናው የሚከተሉትን ርዕሶች ያካትታል፡- የፆታዊ ትንኮሳ ትርጓሜ/ፍቺ፤ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ፕሮግራሞች ወይም ተግባራት የሚያካትቷቸው ነገሮች፤ Title IX ምርመራ እንዴት ማካሄድ እንደሚገባ፣ ክስ የሚሰማበት ሁኔታ፣ አቤቱታዎችን እና ኢ-መደበኛ የውሳኔ ሂደቶችን፣ እንደአግባብነቱ ከወገንተኝነት ነፃ ሆኖ እንዴት ማገልገል እንደሚገባ፣ በጉዳዩ ላይ ያሉ እውነታዎችን ስለመገንዘብ፣ ቀድሞ አለመፍረድን፣ የፍላጎት ግጭትን እና መድሎን ማስወገድን ጨምሮ ስልጠና ይሰጣል።

C. የስልጠና ግብዓቶች/ይዘቶች በፆታ ላይ በሚንፀባረቁ የተሳሳቱ አስተሳሰቦች ላይ አይመረኮዙም። የስልጠና ግብዓቶች/ይዘቶች ለፆታዊ ትንኮሳ መደበኛ አቤቱታዎች ከወገንተኝነት ነፃ የሆኑ ምርመራዎችን እና ውሳኔዎችን መስጠትን ያጎለብታሉ።

D. የስልጠና ግብዓቶች/ይዘቶች MCPS ድረ-ገፅ ላይ በይፋ ይገኛሉ።

***ተዛማጅ ምንጮች፡-*** Title IX 1972 የትምህርት ማሻሻያ ህግ፣ በትሻሻለው መሰረት፤ የሜሪላንድ አባሪ ህግ፣ የትምህርት አንቀፅ §7-424፤ የመግባቢያ ሰነድ[2]፤ MCPS የተማሪ ስነምግባር ደንብ

***የዚህ ደንብ ታሪክ፡-*** አዲስ ደንብ፣ ፌብሩዋሪ 17፣ 1993፤ ተሻሻለ ፌብሩዋሪ 22፣ 2006፤ ተሻሻለ፥ ጁላይ 31፣ 2017፤ ተሻሻለ፥ ፌብሩዋሪ 1፣ 2023 ተሻሽሏል።

---

[2] ሙሉ ርዕስ፡- የህግ አስፈፃሚን ተሳትፎ የሚያካትቱ ክስተቶች ላይ የሪፖርት ማድረጊያ ፕሮቶኮሎች/አሰራር ቅደም ተከተሎች በዝርዝር የተቀመጡት፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ ዲፓርትመንት እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ እና በሌላ ኤጀንሲዎች መካከል የማህበረሰብ ተሳትፎ ኃላፊ ፕሮግራም እና ት/ቤት-መሰረት ላደረጉ ክስተቶች ሌላ የህግ አስፈፃሚ ምላሾችን በሚመለከት የመግባቢያ ሰነድ፣ አፕሪል 4፣ 2022። (የመግባቢያ ሠነድ)

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፦ ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

<table>
<tr><td>MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td><td>MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">"Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፦ U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፦ 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ጁን 2022